# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 34

መስከረም 29 ቀን 2015 ዓም(09-10-2022)

ያሳለፍነው ሰሞን ከሌላው ጊዜ የተለዩ ሳይሆን በተመሳሳይ ድብልቅልቅ ባለ ሁኔታ ውስጥ ስለሆነ ደጋግመን አንስተን በመተቸት  የአድማጮቻችንን ጊዜ ላለማባከን ስንል በአንድ እርእስ ላይ ብቻ እናተኩራለን።ይህ እርእስ ለብዙ ጊዜ በሕዝብ ዘንድ ሲጮህለት የኖረው ሰላም የሚለው ቃል ነው።

ለመሆኑ ሰላም ማለት ምን ማለት ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብስ ሰላም ሲል ምን ማለቱ ነው? ሰላሙ በማንና መቼ፣እንዴትስ ደፈረሰ?ብሎ መጠዬቅና መልስ መስጠት ተገቢና አስፈላጊ ነው።እኛም ይህንን እርእስ እያነሳን ብዙ ብለንበታል።በቅርቡም በነበረን ስርጭት  ላይ ስለሰላም አስፈላጊነት መናገራችንን አድማጮች ያስታውሱታል ብለን እንተማመናለን።በዚያው ስርጭታችን ክፍለጊዜ ሰላም ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ለአራዊትና አእዋፋት ጭምር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸናል።

በአጭሩ ሰላም ማለት ካለምንም እረብሻ፣ስጋትና ጥቃት ህይወትን (ኑሮን) መምራት ማለት ነው።እረብሻ ስጋትና ጥቃት በሌላ አካል ወይም በተፈጥሮ ለውጥና እንቅስቃሴ ሊከሰት እንደሚችልም አብራርተናል።ከዚህ ሁሉ ሰፊ ይዘት ካለው የሰላም መናጋት ውስጥ በሰው ልጆች በተለይም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሰላም እጦት እንዴት ተከሰተ ወደሚለው እርእስ በማምራት የበኩላችንን እይታ ልናስቀምጥ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኖረበት ዘመን ጀምሮ ሰላማዊ ኑሮ ኖሯል ለማለት አንደፍርም።የተፈጥሮ ለውጥና እንቅስቃሴ በሚያመጣው መከራና ችግር ሰላማዊ ኑሮው ተናግቶበት ለልዩ ልዩ ችግሮች ተጋልጦ ኖሯል።አንዱን ችግር ሲያልፈው ሌላው እዬተተካ የሰከነ  ሰላማዊ ኑሮ ሊመራ አልቻለም። በመሬት መንቀጥቀጥ፣መንሸራተት፣በድርቅ፣ለርሃብና ቸነፈር፣ለስደት ኑሮ  ሲጋለጥ ኖሯል።አሁንም ከዚያው የተፈጥሮ ፈተና አልተላቀቀም።ይህ ዘመን ተሻጋሪ የሆነ በተፈጥሮ መዛባት የሚከሰት  ችግር እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝብ በጠቅላላው ደስተኛና ሰላማዊ ኑሮ ይኖራል ማለት ዘበት ነው። የተፈጥሮ አመጣሹን ችግር የሚያባብሰው የሰው ልጅ በሚፈጥረው ድክመትና ስግብግብነትን ምክንያት ያደረገው የተፈጥሮን ሚዛን በማናጋቱም እንደሆነ በመስኩ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሊቃውንት በማስረጃ አረጋግጠዋል።

ሌላው ትልቁ የሰላማዊ ኑሮ ጸር የሆነው የሰው ልጅ ወይም የአንድ አገር ሕዝብ በጥቅምና በራስ ወዳድነት ምክንያት እርስ በርሱ የሚጋጭበት ሁኔታ መኖሩ ነው።ይህ በጥቂት ሰዎች ቀስቃሽነት የሚከሰት የሰላም መናጋት ሰው ሰራሽ እንጂ ከሰው አቅምና ችሎታ ማነስ የሚከሰት ተፈጥሮያዊ ክስተት አይደለም።በዚህ ሰው ሰራሽ ችግር ውስጥ ብዙ የዓለም ሕዝብ አልፏል አሁንም እያለፈ ነው።ሆኖም ግን የዓለም ሕዝብ እንደዬአቅሙ ችግሩን ለመቋቋምና አደጋውን ለመቀነስ ጥረት ማድረጉን አላቆመም፤ በዚህም ትንሽ የማይባሉ መፍትሔዎችን ለመፍጠር ችሏል።ስለሆነም ፈተናና ችግር የአዲስ ብልሃትና ጥበብ መገኛ ነው የሚለው ትክክለኛ አባባል እንደሆነ ሁሉም የተቀበለው ሃቅ ነው።እኛ ኢትዮጵያውያን “ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች”! ስንል ፈረንጆችም “ Necessity is the mother of invention”ይሉታል።አዎ ችግርን ቁጭ ብለው ሲያስተናግዱት መኖር መከራውን አያስግደውም፣የግድ መፍትሔ መፈለግን ይጠይቃል። የታደሉት አገሮች በጋራ ጥረታቸው የገጠማቸውን የሰላም መናጋት

ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በከፊል በማሶገድ እፎይታ ቢያገኙም አንዳንድ አገሮችና ሕዝቦች የገጠማቸውን ሰው ሰራሽ ችግር ማሶገድ ተስኗቸው ፣በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ተማግደው፣ብዙ ህይወት እንደጠፋና ያገር ሃብት እንደወደመ ከዚያም በላይ በቋሚ ጠላትነት በሰላም የማይኖሩበት ሁኔታ የፈጠረ የመበታተን አደጋ እንደደረሰባቸውም የሚካድ አይደለም።

ከላይ ጠቆም እንዳደረግነው ሰላም የሚነሳ ችግር በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሊከሰት እንደሚችል በጥቂቱም ቢሆን አሳይተናል።በነዚህ ምክንያቶች የሚፈጠረውን ችግር ከአገራችን ከኢትዮጵያና ከሕዝቧ ጋር ያለውን ትስስር ስንቃኘው የሚከተለውን ይመስላል።

ኢትዮጵያ እንደቀሩት የዓለም ክፍለሃገሮች በተፈጥሮ ለውጥ ምክንያት ለልዩ ልዩ ፈተናና ችግሮች ስትጋለጥ እንደኖረች ሁሉ አሁንም ዬተጋለጠች መሆኗ የሚካድ አይደለም።አንዳንድ አገሮች ለተመሳሳይ ችግር መፍትሔ ሲያገኙለትና ጉዳቱን ሲቀንሱ ያልታደለችው አገራችን ግን ለዚያ የሚያበቃት የሥርዓትና የሕዝብ አንድነት ባለቤት ስላልሆነች ከልመናና ከተዳጋጋሚ ቀውስ ልትወጣ አልቻለችም።በዚያም የተነሳ ሕዝቧ ሰላማዊ ኑሮ ሊመራ አልቻለም።የሰፊ ለም መሬት፣ የብዙ ወንዞችና ጅረቶች ባለቤት የሆነው ሕዝብ በሰላም እጦት ምክንያት ማምረት አቅቶት በርሃብና ቸነፈር የሚታወቅና ለልመና እጁን የሚዘረጋ ሆኗል። ከዚሁ ጋር የተያያዘው ሰውሰራሹ ሰላም ነሹ ችግር በጉልበት የአገሪቱን መንግሥታዊ ተቋም በፈረቃ የሚቆጣጠሩ አምባገነኖች መኖራቸው ነው።እነዚህ መንግሥታት ለሥልጣናቸው እንጂ ለሕዝቡ ሰላማዊ ኑሮ የሚጨነቁ አይደሉም።ችግሩን ከማሶገድ ይልቅ በችግር ላይ ችግር እዬቀፈቀፉ ሰላሙን ነስተውታል።ለባለሥልጣኖቹ የሕዝቡ ሰላም ማጣቱና ቀውስ መፈጠሩ የሚጠቀሙበት አንዱ ዕድል ነው።በተለይም ላለፉት 32 ዓመታት በሥልጣኑ ላይ የተቀመጡት አረመኔዎችና እራስ ወዳዶች ሕዝቡን ከፋፍለው ከሚመስላቸው ጎሳ ጋር በመጣበቅ ለተወለዱበት ጎሳ ተወላጅ ተቆርቋሪ በመምሰል የችግሩ ሁሉ ምንጭ ሌላው ጎሳ እንደሆነ አድርገው በመቀስቀስ እርስ በርሱ እንዲጋጭና እንዲጋደል በማድረግ በጎሳ ገመድ ተብትበውታል። የማመዛዘን ዕድል ያላገኘው ዜጋ በተዘጋጀለት የጥፋት መንገድ እዬነጎደ የሌላውን መሰል የሰው ልጅ የሆነውን በብዙ የጋራ እሴቶች የተሳሰረውን፣አብሮ የኖረውንና ተጋብቶ የተዋለደውን ያገሩን ልጅ በጠላትነት ፈርጆ ሰላማዊ ኑሮውን ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም እዬቀጠፈ የሚኖር ጨካኝ አውሬ ሆኗል።

እነዚህ የሰላም ጸር የሆኑ ቡድኖች ግን ሁሉንም ግፍና በደል የሚፈጽሙት በሰላም ስም ነው። ማን ነበር ኦ ሰላም በስምሽ ስንት ግፍ ተሠራ? ብሎ የጠዬቀው ኢትዮጵያዊ ጸሓፊ?እኛም ሰላምን በስምሽ ስንት ግፍ ተሠራ ብለን እንጠይቃለን።አሸባሪው ለሚያካሂደው ሽብር፣ ጎሰኛው በጎሳው ሥም ሥልጣን የሚወጣበት መሰላል አድርጎ የሚጠቀምበት ስልቱ ሰላም ፈላጊ መስሎ ነው።ለነዚህ ጸረ ሰላም ሃይሎች ሰላም ማለት እነሱ የሚፈልጉትን ለማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር ማለት ብቻ ነው።ለነሱ ሰላም ማለት ከሌላው ጋር አብሮ መኖር ሳይሆን ተለያይቶ ፣ቢቻል አስገብሮና አምበርክኮ አለያም ደብዛውን አጥፍቶ ካለምንም ተቀናቃኝ ወይም ያገር ባለቤት ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ማደር ማለት ነው።

የአምባገነኖቹ ጎሰኛ ቡድን ዓላማ የማይመቸውና በጠላትነት የተፈረጀው ዜጋ በኢትዮጵያ አንድነትና በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው፣ሁሉንም ዜጋ ያገሬ ልጅ ፣ወገኔ ብሎ የሚቆጥረው የአማራው ማህበረሰብ ነው።ይህንን ማህበረሰብ በሚኖርበት ሁሉ እያሳደዱ መግደልና ከአያት ቅድመአያቶቹ የተረከበውን መኖሪያ መሬቱን ነጥቀው ለመውሰድ ያላደረጉትና ያልፈጸሙበት ግፍ የለም።በዬቀኑ በጥይት እዬተደበደበ የሚሞተው፣የሚቆሰለው፣ንብረቱን ተቀምቶ የሚፈናቀለው ሕዝብ ቁጥር በአሃዝ ከሚገልጹት በላይ ሆኗል።

አማራው ከምድረገጽ መጥፋት አለበት የሚለው አቋማቸው የወያኔ መራሹ ኢሕአዴጎችና የኦነግ ኦህዴድ መራሹ ብልጽግና የጋራ መመሪያቸው ነው። በወለጋና በሌሎቹ ያገራችን ክፍሎች ብቻ ሳይሆን አማራው በብዛት በሚኖርባቸውም ክፍላተሃገርና በዋና ከተማዋ በአዲስ አበባ ሳይቀር የጥፋት ዘመቻዎች በስፋት በመቀጠላቸው የአማራው ተወላጅ ሰላማዊ ኑሮ ሊገፉ አልቻለም። በዚህ ስነልቦና የተፈጠረው የህወሃት ኢሕአዴግና የኦነግ ብልጽግና ጥምረት ኢትዮጵያን ቢቻል ጠቅልሎ ካልተቻለም ተቀራምቶ ለማፍረስ የሚያደርጉት ግብግብ ላለፉት 32 ዓመታት ሕዝቡን ሰላም አሳጥቶታል።አሁንም በሰላም ስም የራሳቸውን ፍላጎት ለማስከበር እላይ እታች እያሉ ነው።በዚህ እሩጫቸው ዓለም አቀፍ አጋሮቻቸውም የጨዋታው ተካፋይ ሆነዋል።ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የውስጥና የውጭ ተዋንያን መጫወቻ ሆነዋል።

ይህንን ተገን በማድረግ ኢትዮጵያን ለዘመናት ሲተናኮሉ የኖሩት ግብጽና እረዳቶቿ የበኩላቸውን በማድረግ የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝቡን ሰላም ሲፈታተኑት ኖረዋል፤አሁንም እዬተፈታተኑት ነው።በወያኔና በኦነግ ትከሻ በኩል የጥፋት ክንዳቸውን ዘርግተዋል።የምዕራቡ አገሮችም ከቻይናና ሩስያ ጋር ባላቸው የጥቅም ግብግብ አህጉሩን ለማመስ ካላቸው እቅድ ኢትዮጵያና ኤርትራን በመዳፋቸው ውስጥ ለማስገባት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።ለጥቅማቸው ሲሉ አገር ቢፈራርስ፣ሕዝብ ቢጨራረስ ደንታ አይሰጣቸውም።ለነሱ ጥቅም ከቆመ ፋሽስት የሆነ ድርጅትም ሆነ በሥልጣን ላይ የተቀመጠ ቡድን ዴሞክራት ነው።የሰላም አጋራቸው ነው።ለነሱም በነጻ የሚርመሰመሱበት ሁኔታ መፍጠር የሰላም መስፈን ምልክት ማለት ነው።

በሥልጣን ሽኩቻ ሲራኮቱ የቆዩት ሁለቱ ጸረ ኢትዮጵያ፣ጸረ ኢትዮጵያውያንና ጸረ ሰላም የሆኑት ቡድኖች ላለፉት ሁለት ዓመት በቀሰቀሱት የጥቅምና የሥልጣን ጦርነት ብዙ ንጹሃን ዜጎች ህይወታቸው ተቀጥፏል፤አሁንም እዬተቀጠፈ ነው።አያሌ ያገር ሃብትና ንብረት ወድሟል፤አሁንም እዬወደመ ነው።በዚህ ጸረ ሰላም እንቅስቃሴ ውስጥ የተማገዱት ወንጀለኞች አሁን ስለሰላም እያወሩ የሕዝቡን ልብ ለማማለል ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው።ከላይ እንደጠቀስነው ለእነሱ ሰላም ማለት የሚፈልጉትን እስካገኙ ድረስ ብቻ ነው።ካለማንም ተቃዋሚ ሥልጣኑንም ሃብቱንም ይዘው እስካዘዙበት ድረስ ነው።ለዚያ የሕዝቡ ስቃይ፣መሞት፣መፈናቀል ትርጉም የለሽ ነው።እንደውም የሚከፈል መስዋእትነት ብለው ይቆጥሩታል።የሰላም ድርድር ሲሉም በነጠላ ካልተቻለ በጋራ ሥልጣኑን መቆጣጠርና የሚፈልጉትን እንዳሻቸው የመዝረፍ መብታቸው ለሚጠበቅበት ስምምነት ላይ መድረስ ማለታቸው ነው።

ሰላም ፈላጊዎች ቢሆኑማ ኖሮ ሰላም ያደፈረሱት እነሱ መሆናቸውን አምነው፣የዘረጉትን ጸረ ሰላም ስርዓት ለማሶገድ ፈቃደኛና ተባባሪ በሆኑ ነበር። ለአገራቸው ሕዝብ ክብርና ፍቅር ቢኖራቸውማ ኖሮ የሌሎች አፍሪካ አገሮችን ችግር ስትፈታ የነበረችው ኢትዮጵያ የምዕራቡን ጣልቃ ገብነት ሳይሆን ላገራቸው ሽማግሌዎች የእርቅ ጥሪ ጆሮና ልባቸውን በከፈቱና በተቀበሉ ነበር።የብዙ የሃይማኖት አባቶች፣የምሁራንና የአዋቂዎች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ ውስጣዊ ችግሯን መፍታት ተስኗት የውጭ አገራትን በተለይም ለነጻነታቸው ያበቃቻቸውን የኬንያና የደቡብ አፍሪካ ተወላጆች ጣልቃ ሲገቡበትና የሚፈልጉትን ተጽእኖ ሲያደርጉ ማዬትን የመሰለ ውርደት የለም።ምዕራባውያን በአሜሪካ መሪነት የሚፈልጉት ከላይ የገለጽነው ሲሆን ለመድገም ያህል በከባቢዊ ለሚኖራቸው ተጽእኖ አገልጋይ የሚሆን ባርያ መንግሥት ከመሻት በተረፈ ለኢትዮጵያ ጥቅም፣ሰላምና አንድነት ብለው የሚያደርጉት ቀና ድጋፍ አይደለም።ለነሱ ሰላም ማለት ከባቢው ከሩስያና ከቻይናዎች መዳፍ ውስጥ እንዳይገባ ማድረግ ነው።

በምዕራቡም ሆነ በተደራዳሪዎቹ በኩል የሚቀርበው ሃሳብ ችግሩ በሕገመንግሥቱ መሠረት ይፈታ የሚለው ጫጫታ ነው።ሕገመንግሥቱ የዘረጉትን የጎሳ ሥርዓት ያጸናል እንጂ አይቃወምም።ከዚያም

በተረፈ የግጭቱ ማዕከል እንዲሆን የተፈረደበት የወልቃይትና ጠገሌ ፣የራያና አዘቦ ጉዳይ በሕገመንግሥቱ ይፈታ የሚለው ጥያቄ እነዚህን የአማራውን አጽመ-እርስቶች ለወያኔ አሳልፎ ለመስጠት የሚረዳ በመሆኑ ነው።አሜሪካኖችም ነባሩ ሕዝብ ወደ ቦታው ይመለስ የሚሉት ወያኔ አስፍሮ የነበራቸው ደጋፊዎቹ በቦታው ላይ ተመልሰው ሕዝበ-ውሳኔ ተደርጎ ሚዛኑን ይደፋል ከሚለው አሻጥር በመነሳት ነው።በወያኔ የተያዘው ለም መሬት በሕገመንግሥቱ መሠረት ሕዝበውሳኔ ተከትሎ ሳይሆን በጉልበት የተያዘ መሆኑን ወያኔዎቹም አይክዱም።ስለሆነም አሁን በሕገመንግሥቱ መሠረት ሕዝቡ ይወስን የሚለው ጫጫታ ተቀባይነት የለውም። የመሬቱ ባለቤት የሆነው ነባሩ ሕዝብ በጉልበት የተነጠቀውን በጉልበቱ አስከብሯል፤በቃ!። ይህ ማለት ሌላው ኢትዮጵያዊ የትግራይ ተወላጆችንም ጨምሮ በቦታው ላይ የመኖር መብት የላቸውም ማለት አይደለም።ሁሉም በእኩል ደረጃ  ግዴታው ካሟላ መብቱ ተከብሮ ለመኖር ይችላል።ወያኔ በነዚህ ቦታዎች ላይ እርር ድብን የሚለው የመገንጠሉ ዓላማ ከቦታዎቹ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው።ያንን መንፈግ ማለት ዓላማውን በማምከን የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ልዑላዊነት ማስከበር  እንደሆነ መታዬት አለበት።ወያኔ ወልቃይትና ጠገሌን ፣ራያና አዘቦን ያዘ ማለት እንደ አገር ሊቆጠር የሚያስችለውን አቅም ያዘ ማለት ነው።በቀጥታም በሱዳን በኩል መውጫና  መግቢያ በር አገኘ ማለት ነው።ያም የሁመራን ለም መሬት መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን ኤርትራንም ውጦ የምዕራባዊያንን ፍላጎት ለማስፈጸም የሚችልበት የታማኝነት ውል የሚፈራረምበት ዕድልና አቅም አገኘ ማለት ነው። የድርድሩም መነሻና መድረሻ ይኸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለን።የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም አማራው ይህ እንዳይፈጠር ተባብሮ የአገር አጥፊዎቹን ፣የወያኔንና የኦነግን ቅስም መስበር ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በምዕራባዊያን ሸንገላ ተጃጅሎ ለዘለዓለሙ ባርነት እጁን መስጠት አይኖርበትም። በአፍሪካ ህብረት  በኩል የምዕራባውያን ተንኮል እንደሚሸረብ እወቅ።ጥቁር ስለሆኑ ለፈረንጆች ጥቅም አይቆሙም አትበል።የአፍሪካ ጠላቶች አፍሪካውያን መሪዎች መሆናቸውን አትዘንጋ።ኡሁሩ ኬንያታም ቢሆን ከግሉና ከአገሩ ጥቅም በላይ ለኢትዮጵያ ጥቅም ይቆማል ብለህ አታስብ።ከኢትዮጵያ አለመረጋጋት ጋር የተያያዘ በጉጉት የሚጠብቁት እንዳለ ተረዳ።

ኦነግም ሆነ ወያኔ በዚህ የጋራ ኢትዮጵያን  የማፈራረስ የጋራ አጀንዳ  ላይ ከማይስማሙበት ይልቅ የሚስማሙበት ይበዛል።የጥቅም ግጭታቸውን  በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን በተለይም በአማራው ኪሳራ ሊያካክሱት ይችላሉ።ለዚህ ድርድርና ስምምነት አያስፈልጋቸውም፤ሳይነጋገሩ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።።።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔና ከኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የድርድር ሂደት ምን ይጠብቃል?እነዚህ በጥቅም የሚራኮቱ ቡድኖች ተፋቀሩም ተራራቁም የሚያገኘው ጥቅም የለውም።ሰላምና መብቱን የነፈጉት እነሱ ስለሆኑ ለችግሩ ጠብ የሚል መፍትሔ ይዘውለት አይመጡም።ለሰላሙም ሆነ ለመብቱ ዋስትና የሚሆነው እነዚህ ጠላቶቹ ሲወገዱለት ብቻ ነው።ያንንም ሊያደርግ የሚችለው ተባብሮ ሲታገል ብቻ ነው።

እነዚህ እኩይ ቡድኖች ንብረቱን እዬዘረፉ አደህይተውታል፤በጎሳ ለያይተው አጋድለውታል፤ለስደትና ለመከራ አጋልጠውታል።አፈናቅለውታል፤ብሔራዊና ሰብአዊ ክብሩን ገፈውታል።የሌሎች መሳቂያና መሳለቂያ አድርገውታል።የጥቁር ዘር ማፈሪያ አድርገውታል።ከነዚህ ጨካኞች ምን አይነት ሰላም ይገኛል?በጭራሽ!እነሱ በከተማም ሆነ በጫካ እስካሉ ድረስ ሰላም ቀርቶ እረፍት አይገኝም።በኢትዮጵያ መሬት ቀርቶ በውጭ አገር ቢኖሩም ኢትዮጵያውያን ሰላም አያገኙም።ሰላም ሊሰፍን የሚችለው የሰላም ጸር የሆኑት ሁሉ እስከወዲያኛው ድረስ ሲወገዱ ብቻና ብቻ ነው።

አሁንም ደግመን ደጋግመን እንላለን!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

በጫንቃህ ላይ ተቀምጠው ለእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት፣የሚቀሰቅሱህን እራስ ወዳዶች አትስማ! ለነሱ ሥልጣንና ጥቅም ብለህ ደምህን አታፍስ!ህይወትህን አትለግስ!ኢትዮጵያዊነትህ የምትከበርበትና የምትኮራበት እንጂ የምታፍርበትና የምትጎዳበት ማንነት አይደለም።ስለሆነም እንደ ቀድሞ አባት አያቶችህ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገህ ያዝ፣አክብረህ አስከብረው። ብዙዎች አገር ሳይሆኑ አገር መሥርተህ መኖርህን ልብ በል። አያት ቅድመአያቶችህ ሊወሩ የመጡትን በጋራ ተባብረው እንደመለሱና አሁን የምትኖርባትን አገርህን ያስረከቡህ የጀግኖች ልጅ መሆንህን አስታውስ፣አንተም እንደነሱ ታሪክ ሰርተህ ለተተኪው ትውልድ አገር አስረክብ።

አባቶችህ የሰጡህ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ የቃል ኪዳን ምልክታቸው መሆኑን አስተውል። ሲኖሩ ማተባቸው ሲሞቱም ከፈናቸው መሆኑን አምነህ አንተም ድገመው።

በየቦታው ደምህ የሚፈሰው የአማራ ተወላጅ ሆይ! እስከመቼ ድረስ የአውሬዎች ቀለብ ሆነህ ትኖራለህ? እስከመቼስ በቆረቆርካት አገር ውስጥ የመኖር መብትህ ተገፎ እንደጠላት ተቆጥረህ ትጠቃለህ? ትሰደዳለህ?የበይ ተመልካች ትሆናለህ?እስከመቼስ ለሰውነት ደረጃ ባበቃሃቸው ውለታ ቢሶች ተንቀህና ተረግጠህ ትኖራለህ?እስከመቼ ድረስ ለከፋፋዮች ተመችተህ፣አንድነት አጥተህ እራስህን በራስህ፣እጅህን በእጅህ እዬቆረጥክ ትኖራለህ?ልብና ወኔህን ምን ሰለበው?ያለህ ምርጫ አንድ ብቻ ነው።ኡኡታና ድረሱልኝ ከሚለው ባዶ ጫጫታ ወጥተህ ሌሎች በደረሱበት ሲሆን በልጠህ መገኘትትና መብትህን ለማስከበር በምትችልበት ቁመና ላይ መገኘት ነው።ተበታትነህ የምታደርገው የግለሰቦች የጭፍራ ትግል እንደማያዋጣህ ተረድተህ በአንድ ማእከላዊ አመራር ባለው ድርጅት ትግልህን ብታቀናጀው የድል ባለቤት ትሆናለህ፤አገርህንም ከመበታተን ታድናለህ።በውስጥህ የሚርመሰመሱትን አድርባዬችን፣ አስመሳዮችንና ከሃዲዎች በማሶገድ የዓላማ ጥራት ያለው ትግል አድርግ።ወዳጅና ጠላትህን በሚገባ ተረዳ።የጮሌዎች መጠቀሚያ አትሁን።ለመከራ የተጋለጡትን ወገኖችህን ለማዳን ተንቀሳቀስ!እስከመቼ ድረስ ስቃያቸውን እዬሰማህ ትኖራለህ?ማንንስ ትጠብቃለህ?ለአንተ ከአንተ በላይ ወዳጅ የለህም።ማን ደረሰልህ?ማንስ ይደርስልኛል ብለህ ትጠብቃለህ?ሌላው ኢትዮጵያዊ ከጎንህ ሊቆም የሚችለው የአንተን ጥንካሬና ቁርጠኝነት ሲያይ ብቻ መሆኑን ተረዳ።ደካማን ልጅ እናቱም ብትሆን አትወደውምና በደካማነትህ የሚያጠቃህ እንጂ የሚጠጋህ እንደማይኖር እወቅ!የሚደፍርህ እንጂ የሚያከብርህ እንደማይኖር ተረዳ።በኢትዮጵያዊነትህ ሁሉንም ሁነሃል፤በአማራነትህ ግን ብቻህን እዬተጠቃህ ነው። ኢትዮጵያዊነትህን ከሁሉም በላይ በተግባር አሳይተሃል።ለሌላው ጎሳ ለተረፈች አገር ስትል ብዙ መስዋእትነት ከፍለሃል።ለአንተ ግን ከቆመልህ ያልቆመልህ ይበልጣል።በመዳከምህ ጀርባውን ሰጥቶሃል።

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ያበረከትካቸውን ማሳያ ይሆን ዘንድ “ተናገር አንተ ሓውልት” ከሚለው በደራሲ ግርማ ታደሰ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1964 ዓም ከሃምሳ አንድ ዓመት በፊት የተጻፈ የግጥም መልእክት ልናስታውስህ እንወዳለን።

ዘሬ ኢትዮጵያዊ ነው!

የወንድ ቅድመ አያቴ ከመንዝ ተነስቶ፣

አድአ ተቀመጠ አንዷት ጋላ አግብቶ።

ያች ጋላይቱ የእኔ ቅድመ አያት፣

ልጅ ወለደችና የእኔን አባት እናት፣

ይህች ሴት አያቴ ካደገች በኋላ፣

ግማሽ ጎኗ አማራ ግማሽ ጎኗ ጋላ፣

ለአቅመሔዋን ስትደርስ በአካል እንዳደገች፣

ካማሴን የመጣ አንድ ትግሬ አገባች።

ትዳሩን አስፋፍተው ሲኖሩ ባንድነት፣

ለትግሬው አያቴ ወንድ ወለደችለት።

ይህ ያያቶቼ ልጅ  ሆኖ የተወለደው፣

የቅልቅል ፍሬው የትግሬው የአማራው እንዲሁም የጋላው፣

ለእኔ አባቴ ነው።

የኔ አባባ ትግሬ አማራና ጋላ፣

ላቅመ-አዳም እስኪደርስ ካደገ በኋላ፣

አዲስ አባ ምትኖር የመጣች ከሶዶ፣

አንዲት ጉራጌ ልጅ በጣም አርጎ ወዶ።

ሲኖሩ ሲኖሩ ሲኖሩ ተዋደው፣

ለመሳም በቅተዋል ይኸው እኔን ወልደው።

ትግሬም ነኝ ጋላም ነኝ፣ጉራጌም አማራ፣

ዘሬ ምን ሊባል ነው? ምን ተብሎ ይጠራ?

ትግሬም፣ጋላም፣ ጉራጌም ፣አማራም አልሰኝ፣

እንደው በደፈናው ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ።

ዘሬም ዜግነቴም ባንድነት አንድ ነው፣

ዘሬን አትጠይቁኝ ዘሬ ኢትዮጵያዊ ነው።

## ኢትዮጵያ የማን ነች?

አስማማውን ጠዬኩ አለኝ ነኝ ጎንደሬ፣

አስመረትን ጠዬኩ አለችኝ ነኝ ትግሬ፣

ሙኔንም ጠዬኳት አለችኝ ሐረሬ፣

አሊንም ጠዬኩት  አለኝ ነኝ ወሎዬ፣

ጎጃሜ ነኝ አለ ቢጠዬቅ ወርቅነህ፣

የጠራሁ ሸዌ ነኝ ብሎ አለ ጀማነህ፣

ዲሳሳም ሲመልስ ወለጋ ነኝ አለኝ፣

ሃበርጋም መለሰ እኔም ከሶዶ ነኝ፣

ገመቹም መለሰ እኔም ነኝ ሲዳሞ፣

ጦናም መለሰና እኔም ነኝ ወላሞ፣

አባ ቱሉም አለ ከፋ ነው አገሬ፣

ቶሎሳም ብሎ አለ አሩሲ ነው ዘሬ፣

ጠይቄ ጠይቄ ይህንን ሁሉ ሰው፣

መልስ አላገኘሁም ልቤን የሚያርሰው።

እኔ የፈለኩት ኢትዮጵያዊ ነበር፣

ሰው አላገኘሁም ይህን የሚናገር።

ደንቆ የገረመኝ ያዘንኩት በዚህ ነው፣

ኢትዮጵያ የማን ነች?ኢትዮጵያዊስ ማነው?

ኢትዮጵያ ማን ነው?ኢትዮጵያ የማን ነች?

ይህች ለምለም አገር እንዴት ትጣል የትም፣

የእኔ ነች የሚል ሕዝብ ባለቤት የላትም?

ማሳሰቢያ ጋላ የሚለው አጠራር በአገራችን የተለመደ ስያሜ እንደሆነና የደርግ ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት በክፍላተሃገርና በማህበረሰቦች ስም ላይ ቅያሬ ሲያደርግ ጋላ የሚለው ስያሜ ኦሮሞ እንደተባለ ልብ ይሏል።የዚህ ግጥም ገጣሚም ከደርግ በፊት በነበረው ሥርዓት  ጊዜ የገጠመው ስለሆነ መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ አልታዬንም።ታሪክ በታሪክነቱ ሳይበረዝ መቅረብ አለበት የሚል የጸና አቋም አለን።የደራሲ ግርማ ታደሰ ብቻም ሳይሆን የአገር ውስጥና የውጭ አገር ታሪክ ጸሃፊዎች ሳይቀሩ በዚህ ስያሜ ብዙ መጻህፍቶችን ጽፈዋል።

ከዚሁ ጋር ትግሬ- ትግራይ፣ሲዳሞ- ሲዳማ፣ወላሞ- ወላይታ፣አዳል- አፋር፣ደራሳ- ጌዴኦ፣አሩሲ- አርሲ፣ ገሙጎፋ-ጋሞገፋ---ወዘተ በመባል የስም ለውጥ መደረጉን እንደ ተጨማሪ ምሳሌ ለማቅረብ እንወዳለን።የአንዳንድ መንግሥታዊ ተቋማትም መጠሪያ እንዲሁ ለውጥ አድርጓል ለምሳሌም ጠ/ግዛት የሚለው ክፍለሃገር፣አገር ግዛት የሚለው አገር አስተዳደር---ወዘተ

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ሰላም ወሳኞቹ እራሳችን ኢትዮጵያውያን ነን!

ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም!!እኛ ያላስከበርነውን ሰላም ሌሎች አያስከብሩልንም!!

ብሔራዊ የእርቅና ሰላም ድርድር በሃገር ሽማግሌዎች ይመራ!ሕዝብ ለሕዝብ ይነጋገር!!